የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፷፯
አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No.67
ADDIS ABABA 17th August, 2015

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፱፻፱/፪ሺ፯ ዓ.ም

ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ........................................ገጽ ፰ሺ፫፻፲፰

**CONTENTS**

Proclamation No. 909/2015

Prevention and Suppression of Trafficking in Persons and Smuggling of Migrants Proclamation .......................................................................Page 8318

**አዋጅ ቁጥር ፱፻፱/፪ሺ፯**

**ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ**

ሕገ-ወጥ የሰዎች በተለይም የሴቶችና ሕጻናት ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል ከጊዜ ወደ ጊዜ ሥር እየሰደደ እና እየተባባሰ፣ ዜጎችን ለአስከፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እና እንግልት እየዳረገ በመሆኑ፣ ችግሩን ለመፍታት በኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፍ ከሚደረገው ጥረት በተጨማሪ የሕግ ማዕቀፉ በመከላከል ላይ የተመሠረተ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የወንጀሉ ተጎጂ ለሆኑ ሰዎች ጥበቃ፣ እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም ሊደረግላቸው እንደሚገባ በመገንዘብ እና ለችግሩ ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ዕድሜያቸውን፣ ጾታቸውንና ልዩ ፍላጎታቸውን ያገናዘበ የተለየ ጥበቃ፣ እንክብካቤ እና ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ በማመን፤

በወንጀል ሕጉም ሆነ በሌሎች ሕጎች የተቀመጡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ከችግሩ ስፋት አንፃር በቂ ምላሽ የማይሰጡ በመሆናቸው እና ወንጀለኞች ላይ ለጥፋታቸው ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት ለመጣል የሚያስችል ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

**PROCLAMATION No. 909/2015**

**A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE PREVENTION AND SUPPRESSION OF TRAFFICKING IN PERSON AND SUMGGLING OF MIGRANTS**

WHEREAS, it has become necessary to introduce a preventive strategy by designing the legal system as a viable alternative besides to economic and social efforts undertaken to alleviate the problems related to human trafficking especially, women and children's trafficking, and smuggling of migrants as it is becoming a very serious crime and increasing from time to time, resulting in grave violation of human rights, grief and suffering of citizens;

WHEREAS, realizing that an appropriate protection, support and rehabilitation to the victims are important and provision of special protection, care and assistance to the most vulnerable groups of society with due consideration to their age, gender and special needs is indispensable;

WHEREAS, the Criminal Code and the provisions stipulated in other laws are not adequately tuned with the depth of the problem, and it has become necessary to promulgate law containing grave punishment which enables to pass proportional sentence against criminals;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 24.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፲፰ (፪) በተደነገገው መሠረት በሰዎች መነገድ የተከለከለ በመሆኑ፣ ኢትዮጵያ የተደራጁ ድንበር ዘለል ወንጀሎችን ለመከላከል የተደረሰውን ዓለም አቀፍ ስምምነት ፈራሚ አገር በመሆኗ፣ ስምምነቱን ተከትለው በወጡት ሕገ-ወጥ የሰዎች በተለይም የሴቶችና ሕጻናት ዝውውር ለመከላከል ለመቆጣጠርና ወንጀል ፈጻሚዎችን ለመቅጣት በወጣው ፕሮቶኮል እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ በየብስ፣ በባህርና በአየር ማስወጣትና ማስገባት ለመከላከል የወጣ ፕሮቶኮልን ያጸደቀች በመሆኗ፣ እንዲሁም ከሕገ መንግስቱ እና ከእነዚህ ዓለም አቀፍ ሰነዶች ጋር የተጣጣመና የተሟላ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፱፻፱/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "ሕገ-ወጥ ሰው አዘዋዋሪ" ወይም "ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር አሻጋሪ" ማለት፦

ሀ) በማንኛውም መንገድ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ ሕግን በመጣስ ወይም በራሱ ፈቃድ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል የፈፀመ ወይም ለመፈፀም የሞከረ፤

ለ) በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር የወንጀል ድርጊት ላይ በአባሪነት የተሳተፈ፤

WHEREAS, trafficking in human being is prohibited as provided under Article 18 (2) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia; as Ethiopia is one of the signatories to the United Nations Convention Against Transnational Organized Crimes; as it has also ratified the United Nations Protocol Against the Smuggling of Migrants by Land, Sea and Air and the Protocol to Prevent, Suppress and Punish Trafficking in Persons especially Women and Children; and it is found important to promulgate a law consistent with the Constitution and these international instruments;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Prevention and Suppression of Trafficking in Persons and Smuggling of Migrants Proclamation No. 909/2015".

2. **Definitions**

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ "human trafficker" or "migrant smuggler" means a person who:

a) by any means, either directly or indirectly, in violation of the law or by his personal initiation, commits or attempts to commit the crimes of Human Trafficking and Smuggling of Migrants;

b) participants as an accomplice in the crimes of Trafficking in Persons and Smuggling of Migrants;

ሐ) ሌሎች ሰዎች በወንጀል ድርጊቱ እንዲሳተፉ ያደራጀ ወይም በተደራጀ የወንጀል ቡድን ውስጥ አመራር የሰጠ፤

መ) ሰዎችን ከመኖሪያ አካባቢያቸው ጀምሮ የተስፋ ቃል በመስጠት ለወንጀል ድርጊቱ ወይም ለስደተኝነት የዳረገ፤

ሠ) በማንኛውም መልኩ የወንጀል ድርጊቱን ያበረታታ፣ የወንጀል ድርጊቱ እንዲስፋፋ ያደረገ ወይም የተደራጀው የወንጀል ቡድን በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ወንጀሎችን ለመፈፀም ማሰቡን እያወቀ ለጋራ ዓላማ በቡድን ለተሰባሰቡ ሰዎች አስተዋፅዖ ያደረገ፤

በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ አገር የሚገኝ ማንኛውም ሰው ነው።

፪/ “የተደራጀ የወንጀል ቡድን” ማለት በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ አገር የሚገኝ ወይም የሚንቀሳቀስ ሆኖ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የገንዘብ ወይም ሌላ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ዓላማ አንድ ወይም ከዚያ በላይ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ወንጀሎችን ለመፈፀም የተሰባሰቡና የሚንቀሳቀሱ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የያዘና ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የሚቆይ የተደራጀ ቡድን ሲሆን በማናቸውም መልኩ በሰዎች ለመነገድ የተቋቋመ ቡድንን ወይም ማህበርን ይጨምራል፤

፫/ “ድንበር ተሻጋሪ የወንጀል ድርጊት” ማለት በዚህ አዋጅ የተደነገገው ወንጀል፦

ሀ) ከአንድ በላይ በሆኑ አገራት የተፈጸመ፤

ለ) በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ የተፈጸመ ሆኖ የድርጊቱ ዝግጅት፣ እቅድ፣ አመራር ወይም የገንዘብ ምንጭ በሌላ አገር የሆነ፤

ሐ) የተፈጸመው በሌላ አገር ሆኖ የድርጊቱ ዝግጅት፣ እቅድ፣ አመራር ወይም የገንዘብ ምንጭ በኢትዮጵያ ከሆነ ወይም በሌላኛው አገር የግዛት ክልል አማካይነት የሆነ፤

c) organizes other people to participate in the crimes or who provides order for organized criminal group;

d) solicits people from their residence to migrate by providing a promise; or

e) in any way encourages, promotes or intentionally gives assistance for persons organized with common motive for the commission of the crime stipulated in this Proclamation;

living either in the territory of Ethiopia or outside.

2/ “organized criminal group” means a structured group of two or more person living and operating in Ethiopia or elsewhere, existing for a limited or unlimited period of time and acting in concert with the aim of committing one or more offences stipulated under this Proclamation, in order to obtain, directly or indirectly a financial or other material benefit, and it includes association and groups organized for trafficking;

3/ “transnational crime” means when the commission of the crimes stated under this Proclamation:

a) involves more than one country;

b) is committed under the territory of Ethiopia with its preparation, planning, direction, supervision or funding in another country;

c) in committed in another country with its preparation, planning, direction, supervision or funding in Ethiopia or through another country;

መ) የተፈፀመው ከአንድ በላይ በሆኑ አገራት በሚንቀሳቀስ የተደራጀ የወንጀል ቡድን የሆነ፤ ወይም

ሠ) በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ ወይም በሌላ አገር የተፈፀመ ቢሆንም የወንጀሉ ውጤት በሌላ አገር ወይም በኢትዮጵያ ላይ የሆነ፤

ድርጊት ነው።

፬/ “ብዝበዛ” ማለት የሚከተሉትን ያካትታል፦

ሀ) በሌሎች ሰዎች ዝሙት አዳሪነት መጠቀም ወይም ሌላ ማንኛውም አይነት ወሲባዊ ብዝበዛን፤

ለ) የጉልበት ብዝበዛ፣ የግዳጅ ሥራ ወይም አገልጋይነት፤

ሐ) ባርነት ወይም ባርነት መሰል ተግባር፤

መ) የወሲብ አገልጋይነትን ጨምሮ ሰውን የማይገባ አገልጋይ ማድረግ፤

ሠ) በመያዣነት መያዝ ወይም አሳልፎ ለሌላ መስጠት፤

ረ) የሰው ልጅን አካል ማውጣት ወይም መውሰድ፤

ሰ) አስገድዶ በልመና ተግባር ማሰማራት፤ ወይም

ሸ) ህፃናትን ለወታደራዊ አገልግሎት ማሰማራት።

፭/ “ባርነት” ማለት የሌላ ሰው የባለቤትነት መብት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እየተፈጸመበት ያለ ሰው የሚገኝበት ሁኔታ ወይም አቋም ነው፤

፮/ “ሰውን በማይገባ አገልጋይ ማድረግ” ማለት አንድ ሰው ሊያስቀረው፣ ሊከላከለው ወይም ሊቀይረው በማይችልበት ሁኔታ አገልግሎት እንዲሰጥ ወይም ሥራ እንዲሰራ ማድረግ ወይም ማስገደድ ነው፤

፯/ “የዕዳ መያዣ ማድረግ” ማለት በሌላ ሦስተኛ ወገን አስቀድሞ በማናቸውም ሁኔታ ግዴታ ለተገባ ወይም ለተጠየቀ ዕዳ የራስን ወይም ኃላፊ የሆነውን ሰው አገልግሎት በመያዣ ከማቅረብ የሚመነጭ ሆኖ የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነትና የጊዜ መጠን ባልተወሰነበት ሁኔታ የሚከሰት ማንኛውንም ዓይነት በሰው ልጅ የመነገድ ተግባርን ታሳቢ የሚያደርግ የመያዣነት ተግባር ነው፤

d) is committed by an organized criminal group engaged in criminal activity in more than one country;

e) is committed under the territory of Ethiopia even another country with its effect in another country or in Ethiopia.

4/ “Exploitation” include the following:

a) benefiting from prostitution of others or other forms of sexual exploitation;

b) labor exploitation, forced labor or servitude;

c) slavery or practices similar to slavery;

d) sexual servitude and enslavement;

e) debt bondage or surrender as pledge for another;

f) removal or taking of organs of the human body;

g) forcefully engaging for begging;

h) engaging children for military service.

5/ “slavery” mean the status or condition of a person over whom any or all the powers attaching to the right of ownership are exercised;

6/ “servitude” means the conditions or the obligations to work or to render services from which the person cannot escape, prevent or alter;

7/ “debt bondage” means the pledging by the debtor of his personal service or labor or those of a person under his control as security or payment for a debt, when the length and nature of service is not clearly defined or when the value of the services as reasonably assessed is not applied towards the liquidation of the debt and resemble trafficking in human;

፰/ "በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር" ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ሰዎችን ዜግነት ወደሌላቸው ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ወዳላገኙበት አገር በሕገ-ወጥ መንገድ በየብስ፣ በባህር ወይም በአየር ማስገባት ወይም እንዲወጡ ማድረግ ነው፤

፱/ "ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን" ማለት እንደ አግባብነቱ የኢትዮጵያ መንግስት በውጭ ሃገራት ያቋቋማቸው ኤምባሲዎች፣ ቋሚ መልዕክተኛ ጽሕፈት ቤት፣ ቆንሲላ ጽሕፈት ቤቶች እና የክብር ቆንሲላዎች ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የውጭ አገር ኤምባሲዎች እና ቆንሲላ ጽሕፈት ቤቶች ማለት ነው፤

፲/ "ስደተኛ" ማለት በስደተኞች ጉዳይ አዋጅ የተመለከቱ መስፈርቶችን የሚያሟላ ሰው ነው፤

፲፩/ "ተጎጂ" ማለት በዚህ አዋጅ የተደነገጉ የወንጀል ድርጊቶች የተፈፀበት ሰው ወይም የወንጀል ድርጊቱ በመፈፀሙ ጉዳት የደረሰበት ሰው ሲሆን ማንኛውንም የሥነ-ልቦና፣ ሞራላዊ፣ አካላዊ ወይም የኢኮኖሚ ጉዳት ወይም ሌላ መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የደረሰበት ሰው ነው፤

፲፪/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ ፵፯ (፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባንና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፲፫/ "ሕጻን" ማለት ዕድሜው ከ፲፰ ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው፤

፲፬/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፍትህ ሚኒስቴር ወይም የፍትህ ሚኒስትር ነው፤

8/ "smuggling of migrants" means an act immigrating or emigrating individuals, in land, see and air, to country of which the person don't have nationality, work or residence permit, with direct or indirect intention to procure financial or material benefit;

9/ "diplomatic mission" means as appropriate, the Embassy, permanent mission, consular office and honorary consul established by Ethiopian government in foreign countries or foreign embassies and consular offices hosting in Ethiopia;

10/ "Refugee" means any person who full fills the criteria's stipulated under Refugee Proclamation;

11/ "victim" means a person against whom the offence stipulated under this Proclamation has been committed or any person who has sustained harm, including mental and physical injury, emotional suffering, economic loss or substantial violation of basic human rights due to the commission of the crime;

12/ "Region" means any state referred to under Article 47 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, and for the purpose of this proclamation, it includes Addis Ababa and Dire Dawa City Administration;

13/ "child" mean any person under the age of 18 years;

14/ "Ministry or Minister" mean, accordingly, the Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice or Minister of Ministry of Justice;

፲፭/ "ፖሊስ" ማለት የፌዴራል ፖሊስ ወይም በዚህ አዋጅ ለተመለከቱ ጉዳዮች የፌዴራል ፖሊስ ሥልጣን በውክልና የተሰጠው የክልል ፖሊስ ነው፤

፲፮/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፯/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት

## ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀሎች

### ፫. ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር

፩/ ማንኛውም ሰው በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውጪ ለብዝበዛ ዓላማ ሲባል፦

ሀ) በአገር ውስጥ ሥራና ሠራተኛን ለማገናኘት ወይም ለሥራ ወይም ለሥራ ልምምድ ወደ ውጭ አገር መላክ በሚል ሽፋን፤

ለ) የጉዲፈቻ ስምምነት በማድረግ ወይም በጉዲፈቻ ሽፋን፤ወይም

ሐ) ለሌላ ማንኛውም አይነት ዓላማ፤

ዛቻን፣ ሀይልን ወይም ሌላ የማስገደጃ ዘዴ በመጠቀም፣ በማገት፣ በመጥለፍ፣ በተንኮል፣ በማታለል ወይም የተስፋ ቃል በመስጠት፣ ሥልጣንን አላግባብ በመጠቀም፣ የሰዎችን ለጥቃት ተጋላጭነት በመጠቀም ወይም ስለሌላው ኃላፊነት ያለበትን ሰው ፈቃድ ለማግኘት መደለያ ወይም ጥቅም በመስጠት ወይም በመቀበል ሰዎችን የመለመለ፣ ያጓጓዘ፣ ያዘዋወረ፣ ያስጠለለ ወይም የተቀበለ እንደሆነ ከ፲፭ ዓመት እስከ ፳፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና ከብር ፻፶ሺ. እስከ ብር ፫፻ሺ. በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የወንጀል ድርጊት የተፈፀመው፦

ሀ) በሕጻናት፣ በሴቶች ወይም በአዕምሮ ወይም በአካል ጉዳተኞች ላይ ከሆነ፤

15/ "police" mean Federal Police or Regional State Police to whom the power of Federal Police is delegated with respect to this Proclamation;

16/ "person" mean any natural or juridical person;

17/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO

## CRIMES OF TRAFFICKING IN PERSONS AND SMUGGLING OF MIGRANTS

### 3. Trafficking in Persons

1/ Any person, for the purpose of exploitation, within the territory or outside of Ethiopia:

a) at the pretext of domestic or oversees employment or sending to aboard for work or apprenticeship;

b) by concluding adoption agreement or at the pretext of adoption; or

c) for any other purpose;

using threat or force or other means of coercion, abduction, fraud, deception, promise, abuse of power or by using the vulnerability of a person or recruits, transports, transfer harbors or receives any person by giving or receiving of payments or benefits to achieve the consent of a person having control over another person shall be punishable with rigorous imprisonment from 15 years to 25 years and with fine from 150,000 to 300,000 Birr.

2/ Where the crime stipulated under sub-article (1) of this Article:

a) is committed against child, women or anyone with mental or physical impairment;

ለ) ተጎጂው ለአካላዊ ወይም አዕምሯዊ ጉዳት ከተዳረገ፤

ሐ) አደንዛዥ ዕፅ፣ መድሃኒት ወይም የጦር መሣሪያ በመጠቀም እንደሆነ፤

መ) በመንግስት ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ ከሆነና ወንጀሉን የፈጸመው የተሰጠውን ኃላፊነት መከታ በማድረግ ከሆነ፤ ወይም

ሠ) በተጎጂው ወላጅ፣ ወንድም፣ እህት፣ አሳዳጊ ወይም በተጎጂው ላይ ሥልጣን ባለው ሰው የሆነ እንደሆነ፤

ከብር ፪፻ሺ እስከ ብር ፭፻ሺ በሚደርስ መቀጮ እና ከ፳፭ ዓመት በማያንስ ፅኑ እስራት ወይም እድሜ ልክ እስራት ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ላይ የተጠቀሱት ልዩ ልዩ መንገዶች በጥቅም ላይ ባይውሉም፣ ህጻናትን ለብዝበዛ አላማ መመልመል፣ ማጓጓዝ፣ ማዘዋወር፣ ማስጠለል ወይም መቀበል ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ነው፡፡

**፬. <u>ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን መደገፍና ማመቻቸት</u>**

ማንኛውም ሰው ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን፦

፩/ እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የራሱንም ሆነ በይዞታው ሥር ያለን ቤት፣ ሕንጻ ወይም ግቢ ለሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ዓላማ ያከራየ፣ እንዲጠቀሙበት የፈቀደ፤

፪/ ለማስፋፋት የተለያዩ የህትመት ውጤቶችን ያባዛ፣ ያጠራቀመ፣ ያሰራጨ፣ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ ወይም ወደ ውጪ ያስወጣ፤

፫/ ለማበረታታት በማሰብ የሥራ ቅጥር ተቋም በማደራጀት ያስተዳደረ፣ የመራ ወይም በገንዘብ የደገፈ፤

፬/ እያወቀ የትራንስፖርት አገልግሎት ያመቻቸ ወይም ተጎጂዎችን በአየር፣ በምድር ወይም በባህር ያጓጓዘ ወይም አገልግሎቱን ያመቻቸ፤

፭/ ለማመቻቸት ሌላውን ሰው የተጭበረበረ፣ ሀሰተኛ ወይም በሕገ-ወጥ መንገድ መታወቂያ ወይም የጉዞ ሰነድ እንዲያገኝ የረዳ፣ እንዲዘጋጅ ያደረገ፣ ያቀረበ፣ ይዞ የተገኘ ወይም እነዚህን ሰነዶች ወደ ሀሰት የለወጠ፤ ወይም

b) resulted in physical or psychological harm on the victim;

c) is committed by using drugs, medicine or weapons as a means;

d) is committed by public official or civil servant in abusing of power; or

e) is committed by a person who is parents, brother, sister, a guardian or a person having a power on the victim;

the punishment shall be rigorous imprisonment not less than 25 years or life imprisonment and with fine from 200,000 to 500,000 Birr.

3/ The recruitment, transportation, transfer, harboring or receipt of a child for the purpose of exploitation shall be considered trafficking in persons even if this does not involve any of the means stipulated under sub article (1) of this article.

**4. <u>Assisting and Facilitating Trafficking in Persons</u>**

For the purpose of promoting human trafficking, any person who:

1/ permits his house building or other permits in his own name or in his control to be used for human trafficking knowingly or ought to have known;

2/ publishes, stores, disseminates, imports or exports any publication;

3/ manages, runs or finances by organizing any job recruitment agency;

4/ knowingly arrange transportation, transport or facilitate the transportation of victim by land, sea or air;

5/ assist, produce, provide, holds and falsifies any fraudulent or false identity card or travel document or assist to get these documents through illegal means for the benefit of other person; or

፮/ ለማመቻቸት የሌላውን ሰው የመንቀሳቀስ ነፃነቱን እንዳይጠቀም ወይም ሕዝባዊ አገልግሎቶች እንዳያገኝ ለማድረግ የተጎጂዎችን መታወቂያ ወይም የጉዞ ሰነድ መያዣ ያደረገ፣ በኃይል የነጠቀ፣ የሰወረ፣ ያጠፋ ወይም እንዲጠፋ ያደረገ፤

እንደሆነ ከ፲፭ ዓመት እስከ ፳፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር ፩፻፶ሺ. እስከ ብር ፫፻ሺ. በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

**፭. ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል**

፩/ ማንኛውም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የገንዘብ፣ ቁሳዊ ወይም ሌላ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ለማስገባትም ሆነ ከኢትዮጵያ ግዛት ለማስወጣት ሲል ድንበር ካሻገረ፣ ድንበር ለማሻገር ከሞከረ ወይም ድንበር ለማሻገር በዝግጅት ላይ ከሆነ ከ፲፭ እስከ ፳ ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራትና ከብር ፩፻፶ሺ. እስከ ብር ፫፻ሺ. በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው የወንጀል ድርጊት የተፈጸመው፦

ሀ) በሕጻናት፣ በሴቶች ወይም በአዕምሮ ወይም በአካል ጉዳተኞች ላይ ከሆነ፤

ለ) ተጎጂውን ለአካላዊ ወይም አዕምሯዊ ጉዳት ከተዳረገ፤

ሐ) አደንዛዥ ዕፅ፣ መድሃኒት ወይም የጦር መሣሪያ በመጠቀም ከሆነ፤

መ) ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ የወንጀል ጥፋተኝነት ሪከርድ ባለበት ሰው እንደሆነ፤ ወይም

ሠ) በመንግስት ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ ከሆነ እና ወንጀሉን የፈጸመው የተሰጠውን ኃላፊነት መከታ በማድረግ ከሆነ፤

በቅጣቱ ከ፳ ዓመት ያላነሰ ፅኑ እስራት እና ከብር ፫፻ሺ. እስከ ብር ፭፻ሺ. በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡



6/ holds as debt bondage, forcefully snatches, conceals, destroys or causes to destroy the victim's identity card or travel documents to restrain his right to movement or access to public service;

shall be punished with rigorous imprisonment from 15 years to 25 years and with fine from 150,000 to 300,000 Birr.

**5. Crime of Smuggling Migrant**

1/ Any person, either directly or indirectly with the intention to procure financial or other material benefit, who causes migrants to cross border, attempts to cross or prepare to cross into or out from the territory of Ethiopia illegally shall be punishable with rigorous imprisonment of 15 years to 20 years and with fine from 150,000 to 300,000 Birr.

2/ If the crime stipulated under sub-article (1) of this Article:

a) is committed against child or women, or any person with mental or physical impairment;

b) causes the victim to suffer a physical or psychological harm;

c) is committed by using drugs, medicine or weapons;

d) is committed by a person who has a similar criminal record; or

e) is committed by public official or civil servant in abusing of power;

the punishment shall be rigorous imprisonment not less than 20 years and with fine from 300,000 to 500,000 Birr.

**፮. ከባድ ሁኔታ**

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፫ ወይም ፭ የተመለከተው የወንጀል ድርጊት በተጎጂው ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ያስከተለ እንደሆነ ወይም ወንጀል አድራጊው ድርጊቱን የፈፀመው የተደራጀ የወንጀል ቡድን አባል በመሆን ወይም ቡድኑን በመምራት ወይም በማስተባበር እንደሆነ ወይም ወንጀሉ የተፈጸመው በስፋትና በብዛት እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ቅጣቱ የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም ሞት ይሆናል፡፡

**፯. መታወቂያ ወረቀትና የጉዞ ሰነዶችን የሚመለከት ወንጀል**

ማንኛውም ሰው ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር በማሻገር ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ለማስገባት ወይም ከኢትዮጵያ ግዛት ለማስወጣት የተጭበረበረ ወይም ሐሰተኛ መታወቂያ ካርድና የጉዞ ሰነዶችን ካዘጋጀ፣ ይዞ ከተገኘ፣ ካቀረበ ወይም ካስተላለፈ ከ፲ ዓመት በማያንስ እና ከ፳ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራትና ከብር ፻ሺ. እስከ ብር ፪፻ሺ. በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

**፰. ሕገ-ወጥ ስደተኛ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ወይም በአገር ውስጥ እንዲቆይ ድጋፍ ስለመስጠት**

በሌላ ሕግ የተደነገገው ቢኖርም የውጭ አገር ዜጋ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንዲቆይ ወይም እንዲኖር ለማድረግ የመኖሪያ ፈቃድ፣ መታወቂያ ካርድና ሌሎች የጉዞ ሰነዶች የሚያስፈልግ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ሕገ-ወጥ ስደተኛ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት እንዲሻገር ድጋፍ የሰጠ ወይም በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የተሻገረ ስደተኛ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንዲኖር ወይም እንዲቆይ የረዳ ማንኛውም ሰው ከ፫ ዓመት እስከ ፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

**፱. በሕገ-ወጥ መንገድ በአንድ አገር ውስጥ እንዲቆይ መተባበር**

ማንኛውም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ፦

፩/ ሕግን በመጣስ ዜግነት ወይም የመኖሪያ ፈቃድ የሌለውን የውጭ አገር ሰው በሕጋዊ መንገድ ለመኖር የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ሳያሟላ በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ኢትዮጵያዊ የሆነን ሰው በሌላ አገር እንዲቆይ የተባበረ፤

**6. Aggravated Circumstance**

Where the offence stipulated under Articles 3 and 5 of this Proclamation results in sever bodily injury or death to the victim, where the offender commits the offence as being a member, a leader or coordinator of an organized criminal group or where the crime is committed in large scale, the punishment shall be a life imprisonment or death penalty, depending on the case.

**7. Offences Related to Identity Card or Travel Documents**

Any person who produces, possesses, provides or transfers fraudulent or false identity card or travel documents to smuggle migrants to enter into and escape from the territory of Ethiopia by land, sea or air, shall be punishable with a rigorous imprisonment not less than 10 years and not exceeding 20 years and with a fine from 100,000 to 200,000 Birr.

**8. Assisting Smuggled Migrant to Enter or Stay in the Territory of Ethiopia**

Notwithstanding the provisions of other laws, any person who, knowingly or where he should have known the importance of residence permit, identity card and other travel documents to foreigner to stay or to live in Ethiopian, assists smuggling of migrants to enter in to Ethiopia or assists the smuggled migrants to stay or to live in the territory of Ethiopia, shall be punishable with rigorous imprisonment from 3 to 5 years.

**9. Assistance to Illegal Stay in any Country**

Any person who, in order to obtain directly or indirectly a financial or material benefit, intentionally:

1/ assist, to stay in the territory of Ethiopia, a foreigner who is not a national or have no residence permit by violating the law and without complying with the necessary requirements to live legally or to stay an Ethiopian national elsewhere in other country;

፪/ ሕግን በመጣስ ሌላን ሰው ወደ ኢትዮጵያ ወይም ወደ ሌላ አገር እንዲገባ ወይም ድንበር አቋርጦ እንዲሻገር ያመቻቸ፣ ወይም

፫/ አድራጊቱ ሰዎችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ለማሻገር መጠቀሚያ ሊሆን እንደሚችል እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ወይም ሊያውቅ የሚችልበት መንገድ እያለ ሐሰተኛ መታወቂያ ካርድ ወይም የጉዞ ሰነድ ለመስጠት የተስማማ፣ የሰጠ፣ ያስተላለፈ፣

እንደሆነ ከ፲ ዓመት እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር ፩፻ሺ. እስከ ብር ፭፻ሺ. በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

## ፲. ማስረጃን ስለማጥፋት ወይም ምስክርነት እንዳይሰጥ ስለማድረግ

ማንኛውም ሰው በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል የምርመራ፣ የክስ ወይም በፍርድ ሂደት ወቅት ጥቆማ ያቀረበን፣ መረጃ የሰጠን፣ ምስክር የሆነን ወይም ምስክር ሊሆን የሚችል ሰውን እንዳይመሰክር፣ የሀሰት ምስክርነት እንዲሰጥ ወይም ማስረጃ እንዲደብቅ በማናቸውም መልኩ ያስፈራራ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መደለያ የሰጠ ወይም ራሱ ማስረጃን ያጠፋ ወይም የደበቀ እንደሆነ ከ፲ ዓመት እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

## ፲፩. ወንጀልን እና በወንጀል ተጠርጣሪን ስለመደበቅ

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ወንጀሎችን የፈፀመን ሰው የደበቀ፣ ወንጀል የተፈፀመበትን ወይም ሊሰራ የታቀደበትን ማንኛውንም ዓይነት ንብረት የሸሸገ ወይም ለወንጀሉ ማስፈፀሚያ የሆነውን ገንዘብ ምንጭ ወይም ከወንጀል ድርጊቱ የተገኘ ማንኛውንም ገንዘብ እንዳይታወቅ ሆነ ብሎ የደበቀ ወይም ምንጩንም ሆነ ገንዘቡ ከወንጀል ድርጊት የተገኘ መሆኑን ማወቅ ሲገባው በማናቸውም መልኩ እንዳይታወቅ ያደረገ ወይም ሳያሳውቅ የቀረ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከ፭ ዓመት እስከ ፲ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

2/ facilitates the smuggling of another person into Ethiopia or to cross the border or to enter into another country by violating law;

3/ agrees to provide, provides or transfers false identity card or travel document, whereby he knows or should have reasonably known or there is a means to know that the document is to be used for the purpose of smuggling of migrants;

shall be punishable with a rigorous imprisonment from 10 years to 15 years and with a fine from 100,000 to 500,000 Birr.

## 10. Destroying of Evidence and Blocking Testimony

Any person who, intimidates by any means or bribes directly or indirectly, an informant, witness or a potential witness not to testify, to provide false testimony or to conceal an evidence in the process of criminal investigation, prosecution or court proceeding of the crime of trafficking in persons or smuggling of migrants or destroys or conceals an evidence by his own, shall be punishable with rigorous imprisonment from 10 years to 15 years.

## 11. Concealing Crime and the Suspected Criminal

Any person who conceals the suspected criminal, who is accused of committing the crimes stipulated under this Proclamation, hides a property used or planed for the commission of the crime or conceals the proceed of the crime or the source of the money used for the commission of crime or disguises or fails to report the source or the money, that he should have known the fact that either the source or money is a proceed of crime, shall be punishable with a rigorous imprisonment from 5 years to 10 years, depending on the cases.

**፲፪. <u>የወንጀል ድርጊቶችን አለማስታወቅ</u>**

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከተ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር የወንጀል ድርጊት፦

፩/ ሊፈፀም የመሰናዳት ተግባር መከናወኑን እያወቀ እና ጉዳት ከመድረሱ በፊት ለመከላከል የሚረዳ ማንኛውም ማስረጃ እያለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም አሳማኝ በሆነ ምክንያት ለማስታወቅ አለመቻሉን ካላስረዳ በስተቀር ያለበቂ ምክንያት መረጃውን ወይም ማስረጃውን ለፖሊስ ወይም ለሌላ አግባብነት ያለው አካል ወዲያውኑ ያልገለፀ ወይም ሐሰተኛ ማስረጃ የሰጠ እንደሆነ በቀላል እስራት ይቀጣል፣ ወይም ይህ የወንጀል ድርጊት ሊያስከትል ይችል የነበረው አደጋ ከፍ ያለ እንደሆነ እስከ ፭ አመት የሚደርስ ፅኑ እስራት ያስቀጣል፤

፪/ በወንጀል ድርጊቱ የተጠረጠረን ወይም ሊፈጽም የተዘጋጀን ሰው ለመያዝ፣ ለመክሰስ ወይም ለማስቀጣት የሚያስችል መረጃ ወይም ማስረጃ እያለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም አሳማኝ በሆነ ምክንያት ለማስታወቅ አለመቻሉን ካላስረዳ በስተቀር ያለበቂ ምክንያት መረጃውን ወይም ማስረጃውን ለፖሊስ ወይም ለሌላ አግባብነት ያለው አካል ወዲያውኑ ያልገለፀ ወይም ሐሰተኛ ማስረጃ የሰጠ እንደሆነ ከ፭ ዓመት የማያንስና ከ፲ ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከብር ፲ሺ. እስከ ብር ፶ሺ. በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

**፲፫. <u>የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት</u>**

፩/ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፺ (፩)፣ (፫) እና (፬) ላይ የተደነገገው ቢኖርም በዚህ ክፍል የተደነገገ ወንጀል የተፈፀመው የሕግ ሰውነት በተሰጠው ድርጅት ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳትፎ ከሆነ፣ ድርጊቱ የተፈፀመው ከተደራጀ የወንጀል ቡድን ጋር በመተባበር ከሆነ ወይም በሰዎች ለመነገድ ወይም በሕገ-ወጥ መንገድ ለማዘዋወር በተቋቋመ ድርጅት ወይም ማህበር ከሆነ፦

**12. <u>Failure to Disclose Criminal Acts</u>**

Whosoever, with regards to the crimes of Trafficking in Persons and Smuggling of Migrants stated on this Proclamation:

1/ having information about the preparation or evidence that may assist to prevent any harm before its commission, fails to immediately inform or give information or evidence to the police or any other competent authority, unless he adduces force majeure or adequate reason prohibiting disclosure, or gives false evidence shall be punishable with simple imprisonment; or if the possible harm of the criminal act is serious, the punishment shall extend to 5 years of rigorous imprisonment;

2/ having an information or evidence capable to arrest, prosecute or punish a suspect or person ready to commit the crime, fails to immediately inform or give information or evidence to the police or any other competent authority, unless he adduces force majeure or adequate reason prohibiting disclosure, or gives false evidence shall be punishable with a rigorous imprisonment not less than 5 years and not exceeding 10 years and a fine of 10,000 to 50,000 Birr.

**13. <u>Criminal Liability of Legal Persons</u>**

1/ Notwithstanding Article 90 (1), (3) and (4) of the Criminal Code of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, where any offence stipulated under this Part is committed by a direct or indirect participation of juridical person, or the crime is committed in cooperation with organized criminal group or through an illegal association or juridical person established for trafficking or smuggling:

ሀ) ለወንጀሉ የተጣለው ቅጣት መቀጮ ከሆነ መቀጮው ከብር ፩ሚሊዮን እስከ ብር ፭ሚሊዮን ይሆናል፤

ለ) ለወንጀሉ የተጣለው ቅጣት የእስራት ቅጣት ከሆነ የቅጣቱ መጠን፦

(፩) እስከ ፭ ዓመት ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር ፭፻ሺ፤

(፪) እስከ ፲ ዓመት ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል ከብር ፭፻ሺ እስከ ብር ፩ሚሊዮን፤

(፫) እስከ ፲፭ ዓመት ለሚያስቀጣ ወንጀል ከብር ፩ሚሊዮን እስከ ብር ፩ሚሊዮን ፭፻ሺ፤

(፬) እስከ ፳፭ ዓመት ፅኑ እስራት እና ከዚያ በላይ ለሚያስቀጣ ወንጀል ከብር ፪ሚሊዮን ፭፻ሺ ያላነሰ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እስከተመለከተው ከፍተኛው ወሰን ለመድረስ በሚችል፤

መቀጮ ይቀጣል።

ሐ) በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ከተደነገገው ቅጣት በተጨማሪ ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ፈርሶ የድርጅቱ ወይም የማህበሩ ማንኛውም ንብረት ወይም ሐብት ይወረሳል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቅጣት የድርጅቱን ወይም የማህበሩን ባለቤት፣ ሥራ አስኪያጅ ወይም በድርጅቱ ስም ወይም ለድርጅቱ ጥቅም ለማስገኘት በማሰብ በድርጊቱ የተሳተፈውን የድርጅቱን ወይም የማህበሩን ሠራተኛ የወንጀል ተጠያቂነት አያስቀረውም።

፫/ የግል ሥራና ሠራተኛ አገኛኝ ኤጀንሲ በሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት ሥራ ላይ ተሰማርቶ እያለ ፈቃዱ በታገደበት ወይም በተሰረዘበት ወቅት ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ለሥራ ወደ ውጭ አገር የላከ እንደሆነ ወይም ሕጋዊ

a) the penalty shall be fine from 1,000,000 Birr to 5,000,000 Birr, where the crime is punishable with fine;

b) when the penalty provided for is imprisonment, the penalty shall be:

(1) a fine not exceeding 500,000 Birr for a crime punishable with not exceeding 5 years rigorous imprisonment;

(2) a fine from 500,000 Birr to 1,000,000 Birr for a crime punishable with not exceeding 10 years rigorous imprisonment;

(3) a fine from 1,000,000 Birr to 1,500,000 Birr for a crime punishable with not exceeding 15 years rigorous imprisonment;

(4) a fine not less than 2,500,000 Birr up to the maximum penalty stipulated under sub-article (1) of this Article when the crime is punishable up to 25 years of rigorous imprisonment and above.

c) in addition to the penalty stipulated under paragraph (a) and (b) of this Article, the juridical person or association shall be dissolved and its property or asset shall be confiscated.

2/ The penalty stipulated under sub-article (1) of this Article shall not relive the criminal liability of the owner or manager of the juridical person or association or the employee participated in the offence on behalf or for the benefit of the juridical person or association.

3/ When a private employment agency engages in employment exchange service send any Ethiopian national abroad for work, while its license is suspended, cancelled or having a licenses but commits or directly or indirectly

ፈቃድ እያለው በሌላ ማናቸውም ሁኔታ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ የወንጀል ድርጊቶችን የፈፀመ ወይም ለወንጀሉ መፈፀም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ማንኛውንም ዓይነት ድጋፍ ያደረገ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገጉትን ቅጣቶች ይቀጣል።

**፲፬. <u>የተጎጂ ፈቃድ</u>**

፩/ ማንኛውም ተጎጂ ብዝበዛ የሚፈፀምበት መሆኑን እያወቀ ፈቃደኝነቱን ቢገልጽም ፈቃደኝነቱ የተገኘው በዛቻ፣ በኃይል፣ በሌላ የማስገደጃ ዘዴ በመጠቀም፣ በመጥለፍ፣ በተንኮል፣ በማታለል፣ ሥልጣንን አላግባብ በመጠቀም፣ የሰዎችን ለጥቃት ተጋላጭነት በመጠቀም ወይም ስለሌላው ኃላፊነት ያለበትን ሰው ፈቃድ ለማግኘት መደለያ ወይም ጥቅም በመስጠት ወይም በመቀበል ከሆነ ሕገ-ወጥ ሰው አዘዋዋሪን ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር አሻጋሪን የወንጀል ተጠያቂነት አያስቀረውም።

፪/ ለሕፃናት ሕገ-ወጥ ዝውውር ወይም ሕፃናት ስደተኞን ከኢትዮጵያ ግዛት ለማስወጣትም ሆነ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ለማስገባት ማንኛውም ሕፃን ወይም የሕፃኑ አሳዳሪ ሕፃኑን በተመለከተ በማንኛውም ሁኔታ ፈቃደኝነቱን የገለፀ ቢሆንም ተቀባይነት አይኖረውም።

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>የመከላከል፣ የምርመራና ክስ፣ የማስረጃና የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች</u>

**፲፭. <u>ጠቅላላ</u>**

፩/ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል የመከላከል፣ የምርመራ፣ ክስ፣ የፍርድ ሂደትና የማስረጃ አሰባሰብ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ይከናወናል።

፪/ የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የወንጀል ሕግ ጠቅላላ ክፍሎች፣ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ወንጀሎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

aids to commit the crimes, in any manner, stipulated in this Proclamation, the punishments specified under sub-articles (1) and (2) of this Article shall apply.

**14. <u>Consent of the Victim</u>**

1/ Notwithstanding to the consent of the victim, for the aim of exploitation, if the consent is secured through a means of threat, coercion, other form of coercion, abduction, fraud, deception, abuse of power or by using the vulnerability or by giving or receiving bribe or benefits to achieve the consent of a person having control over another person, the criminal liability of the human trafficker or migrant smuggler shall not be relieved.

2/ In cases of trafficking of child or smuggling of child from and into Ethiopia, the consent given by any child or his guardian shall be unacceptable.

## <u>PART THREE</u>
## <u>PREVENTION, INVESTIGATION AND OTHER PROCEDURAL PROVISIONS</u>

**15. <u>General</u>**

1/ Prevention, investigation, prosecution, adjudication and evidence collection process of the crime of human trafficking and smuggling of migrants shall be conducted in accordance with the provisions of this Part.

2/ Without prejudice the provisions of this Part, the provisions of the General Part of the Criminal Code, the provisions of Criminal Procedure Code and other relevant laws shall be applicable with respect to the matters not covered in this Proclamation.

**፲፮. ሪፖርት የማድረግ ግዴታ**

፩/ በዚህ አዋጅ ሥር የተመለከቱት ወንጀሎች መፈፀማቸውን ወይም ሊፈፀሙ መሆኑን የሚያውቅ ማንኛውም ሰው፣ የወንጀል ድርጊቱን ለፖሊስ፣ ሌላ አግባብነት ላለው ባለሥልጣን ወይም በአካባቢው ለሚገኝ የአስተዳደር አካል የማሳወቅ እና ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በተመለከተ የወንጀል ድርጊት ምክንያት ወይም በሌላ ማንኛውም ሽፋን በዚህ አዋጅ ለተመለከተ የወንጀል ድርጊት ዓላማ የቤተሰብ አባሉ የሆነ ሰው ከመደበኛው የመኖሪያ አካባቢው የጠፋ መሆኑን ያወቀ ከሆነ ይህንኑ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

**፲፯. ለአደጋ የተጋለጡ ሰዎችን ስለመጠበቅ**

፩/ ፖሊስ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል የተፈጸመ፣ እየተፈፀመ ወይም ሊፈፀም የተቃረበ ለመሆኑ በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው ተጎጂዎችን ለማዳን፦

ሀ) ማንኛውንም ቤት፣ ተሽከርካሪ፣ መርከብ ወይም የመጓጓዣ አውሮፕላን በመፈተሽ ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ፤

ለ) በማንኛውም የአገሪቱ ክፍሎች ወይም ድንበር አካባቢዎች ተገቢውን ፍተሻ በማድረግ ተጎጅዎች እየተዘዋወሩ ወይም ድንበር እያቋረጡ ከሆነ በማዳን ተገቢው እንክብካቤና ድጋፍ ወደሚያገኙበት ቦታ ሊያጓጉዝ፤

ሐ) በከፍተኛ የህመም ስቃይ ውስጥ የሚገኙ ተጎጂዎች ባጋጠሙ ጊዜ በማናቸውም መንግስታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆነ የህክምና ተቋም ውስጥ እርዳታ እንዲደረግላቸው ተገቢውን ትዕዛዝ ሊሰጥ፤

ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፖሊስ የሚወስደውን እርምጃ ወይም የሚሰጠውን ትዕዛዝ ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ማክበርና ማስፈፀም አለበት፡፡

**16. Duty to Report**

1/ Any person who knows the commission or the preparation for the commission of any of the crime stipulated under this Proclamation shall have the duty to notify the police, any other relevant authority or local administrative organ; and shall have duty to take appropriate measure allowed by law.

2/ Any person, who knows that any member of his family is absent due to causes related to the crimes stipulated in this Proclamation or at any other pretext related to crimes stipulated in this Proclamation, shall have a duty to notify same immediately.

**17. Protection of Exposed Persons**

1/ Where there are reasonable suspicions to believe that a crime of human trafficking and smuggling of migrant has been, is being or likely to be committed and with the view to protect victims, the police may:

a) take an appropriate measure by searching any house, vehicle, ship or air planes;

b) conduct proper search in any areas or borders of the country to rescue victims, who are being trafficked or crossing border, and transporting them to care centers;

c) order any governmental and non-governmental medical facility so as to avail proper medical treatment to victims who suffer serious injury.

2/ Any concerned person has the duty to respect and observe order given or any measure taken by the police under sub-article (1) of this Article.

## ፲፰. ልዩ የምርመራ ዘዴዎችን ስለመጠቀም

፩/ ፖሊስ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል የተፈጸመ፣ እየተፈፀመ ወይም ሊፈፀም የተቃረበ ስለመሆኑ ለማመን የሚያስችል በቂ ጥርጣሬ ካለው፦

ሀ) በወንጀሉ የተጠረጠሩ ሰዎች፣ ቡድኖች ወይም ድርጅቶች ውስጥ ሰርጎ በመግባት፤

ለ) በተጠርጣሪዎች ላይ በድብቅ ክትትል ሊያደርግ፤

ሐ) በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት የተጠርጣሪዎችን የግል የመገናኛ ዘዴዎችን ሊጠልፍ፤

መ) የህጋዊ ይምሰል ግንኙነት ሊፈጥር፤ ወይም

ሠ) ሰብአዊ መብትን ባከበረ ሁኔታ ሌላ ተገቢነት ያለው የልዩ የምርመራ ዘዴ በመጠቀም፤

ስለወንጀሉ አፈፃፀም የሚያሳዩ ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሐ) የተደነገገው ቢኖርም አስቸኳይ ሁኔታ ካጋጠመ እና ወንጀሉን በተመለከተ በሌላ መንገድ ማስረጃ ማግኘት የማይቻል መሆኑ ከታመነ ሚኒስትሩ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ፖሊስ የተጠርጣሪን የግል የመገናኛ ዘዴዎች ሊጠልፍ ይችላል፣ ሆኖም ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የግል የመገናኛ ዘዴዎችን የመጥለፍ ተግባር እንዲፈፀም መነሻ የሆኑ ማስረጃዎችና ምክንያቶች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በ፸፪ ሰዓት ውስጥ በፅሁፍ መቅረብና መጽደቅ አለባቸው፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት በሰርጎ መግባት ተግባር ላይ የተሰማራ መርማሪ ወይም በፖሊስ የተመደበ ሰርጎ ገብ በተጎጂዎች ላይ የሰው መግደል ወንጀል ወይም የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ካልፈፀመ በስተቀር ከሰርጎ መግባት ተግባሩ ጋር በተያያዘ ለሚፈፅማቸው የወንጀል ድርጊቶች ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ይሆናል፣ መርማሪ ወይም በፖሊስ የተመደበ ሰርጎ ገብ የሰርጎ መግባት ተግባሩን ከመፈፀሙ

## 18. Applying Special Investigation Techniques

1/ Where there are reasonable suspicions to believe that a crime of human trafficking and smuggling of migrants has been, is being or is likely to be committed, the police may:

a) infiltrate the suspected criminals, criminal groups or organizations;

b) conduct surveillance against the suspects;

c) intercept private communication of the suspects by court order;

d) create simulated legal relationship; or

e) respecting human rights, use appropriate special investigative technique;

to collect evidence proving the crime.

2/ Notwithstanding the provision of paragraph (c) sub-article (1) of this Article, where there is a compelling condition and otherwise than intercepting the communication of the suspects, the police may intercept the communication of the suspect by the order of the Minister; provided, however, that the condition and other evidences opt or initial grounds for interception of communication without court order, shall, in writing within 72 hours, be submitted to and approved by the president of the Federal High Court.

3/ An investigator or police who infiltrates the suspects pursuant to paragraph (a) of sub-article (1) of this Article shall have an immunity from prosecution, unless the police or the investigator causes death on the victim or commits rape. He shall need to sign an agreement, prior to the commencement of his duty, with the Ministry on the list of crimes from which he is immune.

በፊት ከክስ ነፃ ስለሚሆንባቸው የወንጀል ጉዳዮች ያለመከሰስ ስምምነት ከሚኒስቴሩ ጋር መፈራረም አለበት፡፡

፬/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) አፈፃጸም ሲባል ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡

**፲፱. ልዩ መብትን በምክንያትነት መጠቀም ስለመከልከሉ**

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ጥቆማ፣ መረጃ ወይም ማስረጃ የማቅረብ ግዴታን ላለመወጣት ሲል ልዩ መብትን በምክንያትነት መጠቀም አይቻልም፣ ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ቢኖርም ልዩ መብት ያላቸው ሰዎች ሊከሰሱ የሚችሉት ያለመከሰስ መብታቸው በህግ አግባብ ከተነሳ በኋላ ነው፡፡

**፳. ስለመያዝና በእስር ስለማቆየት**

በሌሎች ሕጎች የተደነገጉት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፦

፩/ በዚህ አዋጅ የተመለከቱት በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል የተፈጸመ፣ እየተፈፀመ ወይም ሊፈፀም የተቃረበ ስለመሆኑ ለማመን የሚያስችል በቂ ጥርጣሬ ሲኖር በወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት በተደነገገው መሠረት ፖሊስ ተጠርጣሪዎችን ሊይዝ ይችላል፤

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተያዘ ሰው ምርመራ ያልተጠናቀቀ እንደሆነ በወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት በተደነገገው መሠረት ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ በፍርድ ቤት ሊሰጥ ይችላል፣ ሆኖም በጠቅላላ የሚሰጠው ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ከአራት ወራት መብለጥ የለበትም፡፡

**፳፩. የማስረዳት ሸክም**

፩/ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ የወንጀል ድንጋጌዎች ተጥሰው ፍርድ ቤት የቀረበ የወንጀል ክስን ማስረጃ አቅርቦ የማስረዳት ኃላፊነት የዐቃቤ ሕግ ነው፡፡

4/ For the implementation of sub-article (3) of this Article, the Ministry may issue a directive.

**19. Prohibition of Using a Special Privilege**

1/ Any person can not avail a special privilege regarding the duty to inform, provide information and evidence regarding the crimes stipulated under this Proclamation; failure to comply with his duty shall entail criminal liability pursuant to this Proclamation or any other appropriate law.

2/ Notwithstanding to sub article (1) of this article, any person having immunity shall not be sued before the immunity is lifted in accordance with appropriate law.

**20. Arrest and Detention**

Without prejudice the provisions stipulated in other laws:

1/ police may arrest the suspects in accordance with the provisions of the Criminal Procedure Code, if he has reasonable suspicion that the crimes of trafficking in persons, and smuggling of migrants has been, is being or likely to be committed;

2/ where the investigation on the person arrested pursuant to sub-article (1) of this Article is not completed, court may grant remand in accordance with the provisions of the Criminal Procedure Code; provided, however, that the overall remand period may not exceed four months.

**21. Burden of Proof**

1/ Public prosecutor shall have the burden of proof of criminal cases brought to the attention of court upon violation of the Criminal Provisions of this Proclamation.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫፣ ፬፣ ፭፣ ፮፣ ፲ እና ፲፩ የተደነገጉ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ለሚቀርብ ክስ ዐቃቤ ሕግ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮችን ካስረዳ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ በጉዳዩ ላይ የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሹ እንዲዞር ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ፳፪. <u>በቅን ልቦና ስለሚደረግ ግንኙነት</u>

፩/ በቅን ልቦና በተመሠረተ የውል ወይም በሌላ በማንኛውም መልኩ በተመሠረተ ሕጋዊ ግንኙነት ለሌላ ሦስተኛ ወገን በተላለፈ ማንኛውም ዓይነት ንብረት፣ ገንዘብ ወይም ቁስ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ወንጀሎችን ለመፈፀም ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ ሊወረስ አይችልም፡፡

፪/ ማንኛውም ንብረቱን በሚመለከት በቅን ልቦና ያከራየ ወይም የውል ግንኙነት የፈፀመ ሰው በውሉ ግንኙነት ምክንያት ስለሚመጡ ማናቸውም ኃላፊነቶች ለማወቅ ይችል ዘንድ ተገቢውን መፈፀም አለበት፡፡

## ፳፫. <u>አባሪ ተጠርጣሪን ከክስ ነፃ ስለማድረግ ወይም ቅጣትን ስለመቀነስ</u>

፩/ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል ተካፋይ የነበረ ተጠርጣሪ የወንጀል ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈፀመው ድርጊት እና ወንጀሉን ስለፈፀሙ ተጠርጣሪዎች ጠቃሚ ማስረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆነ በሚኒስትሩ ውሳኔ መሠረት ከክሱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ነፃ ሊደረግ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በወንጀል ድርጊቱ ምክንያት ተጎጂው የሞተ፣ የአካል ክፍሉ የተወሰደ ወይም በማይድን በሽታ የተያዘ እንደሆነ ተጠርጣሪው ከክሱ ነፃ ሊደረግ አይችልም፣ ሆኖም በወንጀል ድርጊቱ የነበረው ተሳትፎን እና በሌሎች ላይ የሰጠውን ማስረጃ ጠቀሜታ ግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣቱ መቀነስ አለበት፡፡

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, upon proof of fundamental facts of the cases, for crimes stipulated under Article 3, 4, 5, 6, 10 and 11 by the public prosecutor, the court, when necessary, may shift the burden of proofing to the defendant.

## 22. <u>Relationship in Good faith</u>

1/ Any property, money or anything transferred to third parties on the basis contract or any other legal relationship with good faith, if used for the commission of crimes stipulated in this Proclamation, it shall not be confiscated.

2/ A leaser who creates contractual relationship in good faith shall have duty to perform appropriate acts so as to have knowledge for any liabilities arising from the contact.

## 23. <u>Suspects Immunity from Prosecution</u>

1/ Any person who involves in the crimes of trafficking in persons or smuggling of migrants and who, before the case is taken to the court, provides substantial evidence as to the offence and other suspects, may be fully or partially set free from prosecution upon the decision given by the Minister.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, when the victim dies, his organ is removed or if he is exposed to incurable disease, the suspect shall not be set free from prosecution; provided however, that depending on his participation and the usefulness of the evidence provided, his punishment shall be reduced.

፫/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ሲባል "ጠቃሚ ማስረጃ" ማለት፦

ሀ) የቀረበው ማስረጃ ብቻውን በቀረበው የወንጀል ክስ የጥፋተኝነት ውሳኔ ለመስጠት በቂ ከሆነ፤

ለ) ማስረጃው በመገኘቱ ሌሎች ማስረጃዎችን ወይም ተጠርጣሪዎችን ለማግኘት መሠረታዊ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል ከሆነ፤ ወይም

ሐ) የተገኘው ማስረጃ ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር በመቀናጀት የጥፋተኝነት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ከሆነ እና ይኸው ማስረጃ ባለመኖሩ ወንጀሉን ለማረጋገጥ በሌላ መልኩ የተሰባሰበው ማስረጃ በቂ የማይሆን ነው ተብሎ ሲታመን፤

ነው፡፡

**፳፬. <u>የዳኝነት ሥልጣን</u>**

፩/ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ወንጀሎች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፪/ የዳኝነት ሥልጣንን የተመለከቱ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፲፫ እና አንቀጽ ፲፯ (፩) (ለ) ድንጋጌዎች ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልንም ያካትታሉ፡፡

**፳፭. <u>ወንጀሉ በይርጋ የማይታገድ ስለመሆኑ</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ እና ፭ የተመለከቱ ወንጀሎችን በፈፀመ ሰው ላይ የሚቀርብ ክስ ወይም ቅጣት በይርጋ አይታገድም፡፡

**<u>ክፍል አራት</u>**

**<u>ስለተጎጂዎች ጥበቃ፣ መልሶ ማቋቋም እና ካሣ</u>**

**፳፮. <u>ተጎጂዎችን ስለመለየትና ስለመታደግ</u>**

፩/ መንግስት አግባብነት ካላቸው የሌሎች አገራት ሚሲዮኖች፣ መንግሥታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት እና ሌሎች ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት ጋር በመተባበር ተጎጂዎችን ለመለየት፣ ለመታደግ፣ ወደ አገራቸው ለመመለስ እና መልሶ ለማቋቋም የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

3/ For the implementation of this Article "Substantial Evidence" means the evidence:

a) is sufficient to bring conviction otherwise than other evidences;

b) Serves as a basis to find out other suspects or to lead to other evidences; or

c) Corroborating other evidences, sufficient to bring conviction and in its absence, conviction is unlikely.

**24. <u>Jurisdiction</u>**

1/ The Federal First Instance Court shall have first instance jurisdiction over offences stipulated under this Proclamation.

2/ The judicial jurisdictions stipulated under Article 13 and Article 17 (1) (b) of the Criminal Code of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shall include crimes of trafficking in persons and smuggling of migrants.

**25. <u>Inapplicability of Statute of Limitation</u>**

The prosecution or execution of sentence of a person who commits crimes stipulated under Article 3 and 5 of this Proclamation shall not be barred by statute of limitation.

**PART FOUR**

**PROTECTION, REHABILITATION AND COMPENSATION FOR VICTIMS**

**26. <u>Identification and Rescue of Victims</u>**

1/ The Government shall put in place necessary working procedures to identify, rescue, repatriate and rehabilitate victims in partnership with other foreign diplomatic missions, concerned government and non-government organizations and other supportive mass organization, the details of which shall be specified by law.

፪/ በሌሎች ሕጎች የተደነገጉ መብቶች እንደተጠበቁ ሆኖ፦

ሀ) ተጎጂዎች የሚደረግላቸውን ጥበቃ፣ እገዛ፣ ድጋፍ እና በፍርድ ሂደት ወቅት ስለጉዳዩ ደረጃ መረጃ እንዲያገኙ፤

ለ) ተጎጂዎች ግላዊ ሚስጥራቸው እና ሰብዓዊ ክብራቸውን በጠበቀ መልኩ በርህራሄና በክብር እንዲያዙ፣ ተገቢው የጤና፣ የማሕበራዊ አገልግሎት፣ ጊዜያዊ መጠለያ፣ የማህበራዊና ሥነ ልቦናዊ ምክር ድጋፍ እንዲያገኙ፤

ይደረጋል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ ሥር የተመለከቱ የወንጀል ጉዳዮችን ለመመርመር፣ ክስ ለማቅረብ ወይም ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የተጎጂዎችን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የተሻለ ድጋፍ እና እንክብካቤ ወደሚያደርጉ ተቋማት መላክ አለባቸው፡፡

፬/ ተጎጂዎች በጊዜያዊ መጠለያ እንዲጠለሉ በሚደረግበት ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ በፖሊስ ጣቢያ፣ በማረፊያ ቤቶች፣ ወይም በማረሚያ ቤቶች እንዲቆዩ መደረግ የለባቸውም፣ በወንጀል ክሱ የፍርድ ሂደት በምስክርነት ካላስፈለጉ በስተቀር በጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ ከሶስት ወራት በላይ መቆየት የለባቸውም፡፡

፭/ ማንኛውም የሌላ አገር ዜግነት ያለው ተጎጂ ጉዳዩ በሌላ አግባብነት ባለው ሕግ የሚታይ ወይም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት በፍርድ ሂደት ለምስክርነት የሚያስፈልግ ካልሆነ በስተቀር በጊዜያዊ መጠለያም ሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ከአንድ ወር በላይ መቆየት የለበትም፡፡

**፳፯. ተጎጂዎችን ወደአገራቸው መመለስ**

በሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር በማሻገር ወንጀል ተጎጂ ሆኖ ከአገር ውጭ የሚገኝ ኢትዮጵያዊን፦

፩/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከተው የኢትዮጵያ ኤምባሲ፣ ከሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣

2/ Without prejudice to the provisions of other laws:

a) victims shall be provided with information on the nature of protection, assistance and support as well as information on any legal proceedings related to them;

b) victims shall be accorded the available health and social services, medical care, counselling and psychological assistance, with care, on a confidential basis and with full respect of privacy.

3/ Organs responsible to investigate, prosecute, adjudicate criminal cases stipulated under this Proclamation shall, taking into account the condition, refer the victim to appropriate organizations and institutions for assistance and support.

4/ The victims while staying at temporary shelter shall, in no case, be kept in police stations, detention centres or prisons; and unless victims are required for testimony in the judicial process, they shall not stay in temporary shelter for a period exceeding three months.

5/ Any person who is not a national shall not stay, either in the temporary shelter or in Ethiopia for more than one month, unless he is required for testimony in the judicial process, or his cases treated in accordance with other relevant laws.

**27. Repatriation of Victims**

Any Ethiopian, found outside of Ethiopia, who is a victim of trafficking in persons and smuggling of migrants:

1/ the Ministry of Foreign Affairs shall, in cooperation with the concerned Ethiopian

ከዓለምአቀፍ ድርጅቶች እና አስፈላጊም ሲሆን ከሌሎች የአገር ውስጥ ተቋማት ጋር በመተባበር ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፪/ ተጎጂው ባለበት አገር የሚገኝ ወይም በቅርበት የሚሠራ የኢትዮጵያ ሚሲዮን ተጎጂው የታሰረ ወይም የተያዘ መሆኑን ካወቀ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተጎጂውን ለመታደግ፣ ተጎጂ በሆነበት የወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ በእስር ላይ የሚገኝ ከሆነ ከእስር ለማስለቀቅ ወይም ወደ አገሩ እንዲመለስ ለማድረግ አስፈላጊውን ይፈጽማል፤

፫/ ተጎጂው በማናቸውም ጉዳይ ባለበት አገር መቆየት ካለበት የሕግ ምክርን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ድጋፎች ከተሟሉ እንዲቆይ ሊያደርግ ይችላል፣ ተጎጂው በሚቆይበት አገር የሚገኘው ወይም በቅርበት የሚሰራው የኢትዮጵያ ሚሲዮን የተጎጂውን አያያዝና የጉዳዩን ደረጃ በመከታተል ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በየወቅቱ ማሳወቅ አለበት።

**፳፰. የውጭ አገር ዜግነት ያላቸውን ተጎጂዎች ወደ አገራቸው ስለመመለስ**

፩/ ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ወደ ኢትዮጵያ የገባ ተጎጂ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፮ (፪)፣ (፫) እና (፬) የተመለከቱ ድጋፎች በሙሉ ይደረግለታል፣ እንደነገሩ ሁኔታ ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ እንዲያገኝ ይደረጋል።

፪/ ማንኛውም በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር በማሻገር ወንጀል ተጎጂ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ በኢትዮጵያ የሚገኝ ከሆነ ወደ ኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ በሕገ-ወጥ መንገድ በመግባቱ ምክንያት በወንጀል ሊጠየቅ አይችልም።

፫/ ለወንጀል ምርመራ፣ ክስና የፍርድ ሂደት ውጤታማነት የውጭ አገር ዜጋ የሆነ በኢትዮጵያ የሚገኝ ተጎጂ ለምስክርነት አስፈላጊ መሆኑ-

Embassy, the Ministry of Labour and Social Affairs, international organizations and, if necessary, with other appropriate domestic organizations initiate the process to return the person in to Ethiopia;

2/ If Ethiopian embassy hosting there or working nearby victim of human trafficking or a smuggled migrant of Ethiopian citizen arrested or detained in a foreign country have knowledge of this occurrence he shall in collaboration with appropriate organs initiate the process to rescue, release and return of the victim to Ethiopian.

3/ if any victim of human trafficking or a smuggled migrant is compelled to stay in a foreign country for any case, the Ethiopian diplomatic mission shall take measures to provide him with legal counselling or assistance; and the Embassy hosting there or working nearby shall follow up handling of the victim and status of the case and periodically report to the Ministry of Foreign Affairs.

**28. Repatriation of Foreign Nationals to their Country**

1/ Any foreign national who is victim and found in Ethiopia shall be fully entitled to the protections mentioned under Article 26 (2), (3) and (4) of this Proclamation, and he shall be provided temporary resident permit, as the case may be.

2/ Any foreign national who is victim of trafficking in persons and smuggling of migrants shall not be criminally liable on his illegal entry into Ethiopian territory.

3/ When a foreign national has been identified as an important witness and if he is willing to testify, in accordance with a relevant law, he

ከታመነ እና ተጎጂው ምስክርነቱን ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆነ የፍርድ ሂደቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ እንዲያገኝ ይደረጋል፣ ሰብዓዊ መብቶቹም በተሟላ መልኩ እንዲከበሩ ይደረጋል፡፡

፬ ስለቪዛ፣ ስለጉዞ ሰነድ እና ሌሎች ሁኔታዎች በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ተጎጂ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ መሆኑ ከተለየ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እና ከሚመለከተው አገር ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ጋር በመተባበር ተጎጂው ወደ አገሩ የሚመለስበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

**፳፱. <u>የተጎጂዎችና ምስክሮች ጥበቃ</u>**

በሌሎች ሕጎች ለተጎጂዎች የተሰጡ ልዩ ልዩ መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል ተጎጂ የሆነ ምስክር እንደነገሩ ሁኔታ በምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፱/፪ሺ፪ የተደነገጉ ጥበቃዎችን እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

**፴. <u>ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ስለመሆን</u>**

ማንኛውም ተጎጂ ለሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል ከመዳረጉ ጋር በተያያዘ በወንጀል አይጠየቅም፡፡

**፴፩. <u>ስለካሣ</u>**

፩/ ፍርድ ቤት በጥፋተኛው ላይ ከሚወስነው ቅጣትና መቀጮ በተጨማሪ ለተጎጂው ወይም በተጎጂው ስም ወጭ ላወጡ ሌሎች ሰዎች ወይም ድርጅቶች ካሣ እንዲከፈል ሊወስን ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚፈከል ካሣ የሕክምና፣ የትራንስፖርት፣ የሞራል ካሳ፣ ከወንጀሉ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ባላቸው ምክንያቶች የደረሱ ጉዳቶች ካሳ እና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው ወጭዎችን ለማካካስ የሚችል መሆን አለበት፣ በማናቸውም ሁኔታ ለተጎጂው የሚከፈል ካሣ እንደነገሩ ሁኔታ ለሕገ-

shall be accorded temporary resident permit, until such time as the proceeding of the court is completed, and his human rights shall be respected adequately.

4/ Without prejudice to the provisions of other laws regarding visa, travel documents and other conditions, when any victim, who is foreign national, is identified in Ethiopian territory, the Ministry of Foreign Affairs in collaboration with relevant authorities and concerned diplomatic mission, shall take appropriate measures to repatriate the victim to the country of origin.

**29. <u>Protection of Witness and Victim</u>**

Without prejudice to different rights stipulated in other laws with respect to victims, any witness, who is a victim of crime of trafficking in persons and smuggling of migrants, shall be entitled with the protections stipulated under Witness and Whistleblowers Protection Proclamation no. 699/2010.

**30. <u>Immunity from Criminal Liability</u>**

Any person victim of trafficking in persons or smuggling of migrants shall not be legally prosecuted on the facts of being a victim of the crime.

**31. <u>Compensation</u>**

1/ The court may decide against the convicted person, in addition to imprisonment and fine, to pay compensation for the victim or to persons or organization who incurred cost in the name of the victim.

2/ The amount of compensation to be paid under sub-article (1) of this Article shall, enable to set off medical, transport, moral damage, any other costs or losses incurred as a direct result of the crime and other appropriate expenses; provided, however, in any case, the compensation shall not be less than the

ወጥ ሰው አዘዋዋሪው ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር አሻጋሪው ከከፈለው ገንዘብ፣ ሊከፍል ከሚችለው ወይም በወንጀል ድርጊቱ ምክንያት ተጎጂው ካጣው ወይም ለሕገ-ወጥ ሰው አዘዋዋሪው ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር አሻጋሪው ካገኘው ጥቅም መጠን ያነሰ መሆን የለበትም።

፫/ ተጎጂው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት ካሣ ማግኘት ያልቻለ እንደሆነ የማካካሻ ክፍያ ከፈንዱ እንዲከፈል ይደረጋል፣ የማካካሻ ክፍያ ተጠቃሚ መሆን የሚችለው ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ተጎጂ ነው።

## ክፍል አምስት
## ስለፈንድ መቋቋም

**፴፪. መቋቋም**

ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ ድንበር ማሻገር ወንጀልን የመከላከል፣ የመቆጣጠር እና ተጎጂዎችን መልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ (ከዚህ በኋላ "ፈንድ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

**፴፫. የገቢ ምንጭ**

የፈንዱ የገቢ ምንጭ ከመንግስት ከሚመደብ በጀት፣ በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚወረሱ ንብረቶችና መቀጮዎች፣ ከግለሰቦች፣ ከልዩ ልዩ መንግስታዊ፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከሚገኝ ልገሳ፣ ከልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የእርዳታ ተቋማት ከሚገኝ ድጋፍ እና ከሌሎች የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከሚያፀድቃቸው የገንዘብ ምንጮች ከሚገኝ ገቢ ይሆናል።

**፴፬. ዓላማ**

ፈንዱ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ የሚከተሉትን ያካትታል፦

፩/ ለተጎጂዎች የሚሰጥ ቁሳዊ እርዳታ ለመደገፍ፤

፪/ ለተጎጂዎች የሚሰጥ የሙያ ሥልጠናን ለመደገፍ፤

፫/ ተጎጂዎችን ለመታደግ፣ መልሶ ለማቋቋም እና ከቤተሰቦቻቸውና ከማሕበረሰቡ ጋር እንዲቀላቀሉ ለማድረግ እንዲሁም ቤተሰቦችን ለማፈላለግ የሚወጡ ወጭዎችን ለመሸፈን፤ እና

amount paid, or to be paid to the human trafficker or migrant smuggler, loss incurred by the victim because of the crime or the benefit obtained by the human trafficker or migrant smuggler.

3/ When the victim cannot get compensation under sub-articles (1) and (2) of this Article, an Ethiopian national can claim a reimbursement payment and shall be paid from the Fund.

## PART FIVE
## ESTABLISHMENT OF FUND

**32. Establishment**

A fund to prevent, control and rehabilitate victims of crime of trafficking in human and smuggling of migrants (hereinafter called the "Fund") is hereby established by this Proclamation.

**33. Sources of Income**

The source of income of the Fund shall be budget allocated by Government, proceeds of sale of properties confiscated or fines imposed as per this Proclamation, voluntary contribution from individuals, governmental organisations, the private sector and charities and societies, grants from different international organization and donors and other financial sources approved by Ministry of Finance and Economy Development.

**34. Objective**

The main objective of establishment of the Fund includes the following:

1/ to assist the provision of material support for victims;

2/ to support provision of professional training to victims;

3/ to cover the expense of relief, rehabilitation, reintegration of victims with their families and community; and

፬/ የተጎጂዎች ጊዜያዊ መጠለያ ግንባታን እና ሌሎች ድጋፎች ለማድረግ።

**፴፭. የፈንዱ አስተዳደር**

የፈንዱ አስተዳደር፣ አሰራርና ፈንዱን የሚያስተዳድረው አካል ተጠሪነት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይወሰናል።

**፴፮. የፈንዱ ተጠቃሚዎች**

በዚህ አዋጅ መሠረት ከተቋቋመው ፈንድ ተጠቃሚ መሆን የሚችለው ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ተጎጂ ይሆናል፣ ሆኖም የሌላ አገር ዜግነት ያላቸው ተጎጂዎች ከፈንዱ ተጠቃሚ ስለሚሆኑበት ሁኔታ መንግስት ሊወስን ይችላል።

**፴፯. የፈንዱ የሂሳብ መዝገብና ኦዲት**

፩/ የፈንዱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራሉ።

፪/ ፈንዱን የሚያስተዳድረው አካል የኦዲት ሪፖርቱን የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ተጠሪ ለሆነለት አካል ማቅረብ አለበት።

**፴፰. የበጀት ዓመት**

የፈንዱ የበጀት ዓመት የመንግስት የበጀት ዓመት ይሆናል።

## ክፍል ስድስት
## የባለድርሻ አካላት ትብብር

**፴፱. ስለብሔራዊ ኮሚቴ መቋቋም**

፩/ የሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር፣ ተጎጂዎችን ለመጠበቅ፣ ድጋፍና የመልሶ ማቋቋም ተግባራትን ለማከናወን እና አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማድረግ፣ በአገሪቱ የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ እቅዶች እና መርሃ ግብሮች የተጎጂዎችን ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን ለማድረግ፣ ወንጀሉ የሚያስከትለው ማህበራዊ ቀውስ፣ በአገር ገፅታ ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተጽዕኖ እና ሌሎች ጉዳዮችን

4/ to support the construction of temporary shelters and other needs.

**35. Management of the Fund**

The management and procedure of the fund and the accountability of the organ which administers it shall be determined by council of ministers regulation.

**36. Beneficiaries of the Fund**

Victims of Ethiopian nationals shall benefit from the Fund established in accordance with this Proclamation; provided; however, the Government shall determine the conditions under which foreign nationals may benefit from the Fund.

**37. Books of Accounts and Audit**

1/ The books of account and other financial records of the Fund shall be audited annually by the Auditor General or by the auditor assigned by him.

2/ The organ which administers the fund shall have the duty to submit the audit report, to the body to whom it is accountable for, within four months following the end of the budget year.

**38. Budget Year**

The budget year of the Fund shall be the fiscal year of the Government.

## PART SIX
## STAKEHOLDERS COOPERATION

**39. Establishment of National Committee**

1/ A national committee, for better coordination of activities designed for victims protection, assistance and rehabilitation, for advising in policy, plans and implementation framework formulations process, to accommodate the interest of victims and for combating the crime of human trafficking and smuggling of migrants; provide with, its basic role to introduce the social impact of the crime and its adverse effect on country's image into the educational curriculum and to maintain the

አስመልክቶ በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ እንዲካተት ለማድረግ፣ ይህንኑ ሥራ በልዩ ልዩ አካላት ዘንድ ለማስተባበር፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን እና አደረጃጀቶችን ፍላጎትና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል ብሔራዊ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

፪/ ብሔራዊ ኮሚቴው በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ ሆኖ የፍትህ ሚኒስቴር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፣ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር እና ሌሎች ልዩ ልዩ የመንግስት ተቋማትን፣ የሃይማኖት ተቋማትን፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን፣ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን፣ ክልሎችን እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ያቀፈ ይሆናል፡፡

፫/ የብሔራዊ ኮሚቴው ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሆኖ ወንጀሉን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ተጎጂዎችን እንደገና መልሶ ለማቋቋም የሚደረገውን ጥረት በአገር አቀፍ ደረጃ ይመራል፤ ያስተባብራል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የብሔራዊ ኮሚቴው አደረጃጀት፣ አባላት አሰያየም፣ ሥልጣንና ተግባር እና የሌሎች ተቋማት ኃላፊነት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፵. ግብረ ሀይል ስለ ማቋቋም

፩/ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ተጎጂዎችን መልሶ ለማቋቋም የሚደረገውን ጥረት የሚደግፍና ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ኮሚቴ የሆነ የፀረ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል የጋራ ግብረ ሀይል (ከዚህ በኋላ "ግብረ ሀይል" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

interest of various social segments and structures shall be established.

2/ The national committee will be lead by the Deputy Prime Minister, and incorporates Ministry of Justice, Ministry of Foreign Affairs, Ministry of Federal Affairs, Ministry of Labor and Social Affairs, Ministry of Women, Children and Youth Affairs, Ministry of Education, Regional States, other governmental organizations, religious institutions, charities and societies, various structures and other respective organizations.

3/ The national committee shall be accountable to the Prime Minister and shall be responsible to lead and coordinate all efforts designed to prevent, counter and rehabilitate the victims at the national level.

4/ Without prejudice to sub-article (2) of this Article, the structure, assignment, power and duties of the national committee and the responsibilities of other institutions shall be determined by a Regulation to be issued by the Council of Ministers.

## 40. Establishment of Task Force

1/ Anti Human trafficking and Smuggling of migrants Task Force (hereinafter called "task force"), which is accountable to the national committee aimed at supporting efforts intended to rehabilitation of victims, prevention and control of crimes of human trafficking and migrant smuggling is established.

፪/ ግብረ ሀይሉ በፍትህ ሚኒስትሩ የሚመራ ሆኖ፦

ሀ. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ የትምህርት ሚኒስቴር፤

ለ. የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የበጎ አድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲ፤

ሐ. በሚኒስትሩ የሚወከል አንድ ኃላፊ፤ እና

መ. በብሔራዊ ኮሚቴው ሰብሳቢ የሚሰየሙ ሌሎች ሰዎችን፤

ያካተተ ይሆናል።

፫/ ግብረ ሀይሉ፦

ሀ. ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት፣ ከአጋር ድርጅቶች እና እንዳስፈላጊነቱ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ተጎጂዎችን ለመጠበቅና ለመርዳት እንዲሁም ወንጀሉን ለመከላከል የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ መርሐ ግብሮችንና እርምጃዎችን በመቅረጽ በብሔራዊ ኮሚቴው ሲፀድቅ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

ለ. ወንጀሉን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ለብሔራዊ ኮሚቴው አቅርቦ ያስፀድቃል፣ የድርጊት መርሃ ግብሩን አፈፃፀም ይከታተላል፣ በየወቅቱ ለብሔራዊ ኮሚቴው ሪፖርት ያቀርባል፤

ሐ. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተጎጂዎችን መልሶ ለማቋቋም፣ ድጋፍ ለማድረግና ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው እንዲኖሩ ለማስቻል ተገቢውን ይፈጽማል፤

መ. ሌሎች በብሔራዊ ኮሚቴው የሚሰጡ ልዩ ልዩ ተግባራትን ያከናውናል።

**፵፩. የፍትሕ ሚኒስቴር ኃላፊነት**

የፍትህ ሚኒስቴር፦

፩/ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ልዩ ልዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር፦

2/ The task force will be led by the Minister of Ministry of Justice and it consists of:

a/ Ministry of Foreign Affairs, Ministry of Labor and Social Affairs, Ministry of Women, Children and Youth Affairs, Ministry of Education and National Security and Intelligence Service;

b/ Ethiopian Federal Police Commission, Charities and Societies Agency;

c/ a representative assigned by the Minister; and

d/ Other individuals assigned by the Chair person of the national committee.

3/ The task force shall:

a/ Design policies, strategies, action plans and measures that enables the protection and assistance of victims in collaboration with appropriate government organs, aid partners, and when necessary, with international organizations and implement them upon approval by the national committee;

b/ Design the national plan of action for the prevention and control of the crime and obtain approval of it from the national committee, supervise its implementation and submit reports periodically;

c/ In collaboration with pertinent stake holders, take appropriate actions for the rehabilitation, assistance and reintegration of victims with the society; and

d/ perform other activities assigned by the national committee .

**41. Responsibility of the Ministry of Justice**

Ministry of Justice shall:

1/ in collaboration with relevant governmental and nongovernmental organizations, shall design an action plan and cause to develop

ሀ) ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀሎችን የሚመለከቱ በተለይም ሕገ-ወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች እና ሕገ-ወጥ ስደተኞችን ድንበር አሻጋሪዎች የሚጠቀሟቸውን የተለመዱ ተጎጂዎችን የመመልመያ ዘዴዎች፣ የብዝበዛና የማቆያ ሥልቶች፣ ተጎጂዎች ተጋላጭ ሊሆኑባቸው ስለሚችሉ የብዝበዛ ዓይነቶች፣ ተጎጂዎች መረጃ እና ድጋፍ ሊያገኙባቸው ስለሚችሉ ተቋማትና የሕግ አስከባሪ አካላት ሚና፣

ለ) ተጎጂዎች ስላላቸው መብት፣ የተጎጂዎችን ደህንነት ለመጠበቅ፣ ለመታደግና ወደ አገራቸው ለመመለስ ስለሚያስችሉ በሥራ ላይ ስላሉ የሕግ ወይም ሌላ መንገዶች፣ ተጎጂዎች መረጃ እና ድጋፍ ሊያገኙ ስለሚችሉባቸው ድርጅቶች፣ ተቋማትና የሕግ አስከባሪ አካላት መረጃ እና ትምህርት የሚሰጡ፣ እና

ሐ) ተጎጂዎች በተለይም ሴቶችና ሕጻናት ለእነዚህ ወንጀሎች እንዲዳረጉ የሚገፋፉ ምክንያቶችን ለማዳከም የሚያስችሉ የግንዛቤ መፍጠሪያ፣

መ) ወንጀሉን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ጥቅም ላይ የዋሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመለየት የማስተዋወቂያ፣

መርሃ ግብሮች፣ አጫጭር ጽሑፎች፣ የማስተማሪያ ሞጁሎች፣ ድራማዎች፣ ሌሎች መሰል የማስተማሪያ ዘዴዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ አስፈላጊ ወጭዎችም ከፈንዱ እንዲሸፈኑ በማድረግ በመገናኛ ብዙሃን እና ሌሎች የግንኙነት አውታሮችን በመጠቀም ለሕዝብ እንዲተላለፉ ያደርጋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገጉት መርሐ ግብሮች እና የመከላከል እርምጃዎች የገጠሩን ማሕበረሰብ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን በአግባቡ ማካተታቸውንና ውጤታማነታቸውንም ለማረጋገጥ በየወቅቱ ግብረ ሀይሉ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል።

broachers, modules, dramatic scenes, and other educational methodologies containing:

a) the recruitment mechanisms of human traffickers and migrant smugglers, means and types of exploitations and other staying mechanisms, the role of law enforcement institutions and other information and support providing institutions;

b) the rights of victims, laws regarding the protection, care and repatriation of Ethiopian nationals who are victims, the role of different organizations, law enforcements and others;

c) the means of minimizing driving forces of victims for such crimes especially about women and children; and

d) best practices used for combating the crime;

and broadcast to public at large through mass medias and other communication means with the costs to be covered from the Fund.

2/ The action plans and measures referred in sub article (1) of this article should include means to access the rural population, provided that, the task force will supervise the implementation.

**፵፪. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊነት**

በሌሎች ሕጎች ለልዩ ልዩ አካላት የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፦

፩/ ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል ጋር በተያያዘ ተጎጂ የሆኑ ሰዎችን ዝርዝር፣ የሚገኙበትን አገር፣ ያሉበትን ሁኔታ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን መረጃ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው ያደርሳል፤

፪/ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል ምክንያት በተለያዩ አገራት ለሚገኙ ተጎጂዎች እና ስደተኞች የየአገራቱን የሥጋት ደረጃ በመለየት በየወቅቱ በተለያዩ የግንኙነት ዘዴዎች እንዲያውቁት ያደርጋል፤

፫/ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል መዳረሻ በሆኑ አገራት የሚገኙ ዜጎች የየራሳቸውን ኮሚዩኒቲ እንዲያቋቁሙ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣ በኮሚዩኒቲው አደረጃጀት መሠረት በየአገራቱ መብትና ጥቅማቸው እንዲከበር ያደርጋል።

**፵፫. የፖሊስ ኃላፊነት**

፩/ ፖሊስ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የብሔራዊ መረጃ ደህንነት አገልግሎት፣ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ወንጀሎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር እንደነገሩ ሁኔታ በምርመራ፣ መረጃ በመለዋወጥ፣ በአቅም ግንባታ እና በመሳሰሉ ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ ይሰራል።

፪/ ፖሊስ ተጎጂዎችን በመለየት፣ ተጎጂዎችን ድንበር ለማሻገር ጥቅም ላይ የዋሉ ንብረቶችን፣ ሰነዶችና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ለመለየት፣ የተደራጁ የወንጀል ቡድኖች የዘረጓቸውን የወንጀል መረቦችና

**42. Responsibility of the Ministry of Foreign Affairs**

Without prejudice to the powers and duties stipulated for different organizations in other laws, the Ministry of Foreign Affairs:

1/ in cooperation with National Intelligence and Security Service and other relevant organs, shall collect and disseminate data's of the list of victims of the crime, the country and the conditions under which they are found and other necessary information's;

2/ shall conduct assessment on trafficking of human and smuggling of migrants and the level of risks of different countries and communicate in different mechanisms to victims and migrants of Ethiopian nationals who reside in other counties;

3/ shall support the establishment of Ethiopian community in the destination countries where crime of trafficking of human and smuggling of migrants found and support the community members to maintain their rights and benefits.

**43. Responsibility of the Police**

1/ Police shall collaborate with Ministry of Justice, National Security and Intelligence Service, Ministry of Labor and Social Affairs and other relevant stakeholders on the areas of investigation, information exchange and capacity building for prevention and suppression of crime stipulated in this Proclamation;

2/ Police may cooperate with internal and similar institutions of other countries, for the identification of victims, the properties used for, the documents and other necessary

ስልቶች ለመለየት ከአገር ውስጥና ከሌሎች የውጭ አገራት መሰል ተቋማት ጋር ግንኙነት ሊፈጥር ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፵፬. ዓለም አቀፍ ትብብር

፩/ ፍትሕ ሚኒስቴር እንደጉዳዩ አግባብነት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር መረጃ መለዋወጥን፣ በጋራ የምርመራ ሥራ ማከናወንን፣ ወንጀለኛ አሳልፎ መስጠትን እና ሌሎች የጋራ የሕግ ትብብርን ጨምሮ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከሌላ ሀገር አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጋር በዚህ አዋጅ እና ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን በሆነችበት ስምምነት እና የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት በሚፈቅደው መሠረት በትብብር ይሰራል፣ ማዕከላዊ ባለስልጣን ሆኖ ያገለግላል፡፡

፪/ ፍትሕ ሚኒስቴር እንደአስፈጊነቱ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ የወንጀል ጉዳዮችን ለመከላከል እና ተጠርጣሪዎችን ለፍርድ ለማቅረብ የሚያስችሉ ስምምነቶችን ከሌሎች አገራት ጋር ልዩ ልዩ የትብብር ማዕቀፎችን ሊፈራረም ይችላል፡፡

፫/ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል ፖሊስ ተመሳሳይ ተልዕኮ ካለው መሰል የሌላ ሀገር ተቋም ጋር እንካ በእንካ መርህ ላይ ተመስርቶ የመረጃ ልውውጥ፣ በሌላ መልኩ የጋራ ትብብር ሊያደርግ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ከሌላው አገር መሰል ተቋም ጋር የመግባቢያ ስምምነት ሊፈራረም ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ሊኖሩ የሚገባቸው የስምምነት ማዕቀፎች አለመፈረማቸው መንግስት የጋራ የሕግ ትብብርና ድጋፍ ለማድረግ ወይም ለመቀበል የሚያስችል አስተዳደራዊ እርምጃ ከመውሰድ አያግደውም፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ ከተደነገገው በላይ ከፍተኛ ቅጣት ሊያስቀጣ ለሚችል ወንጀል ማስረጃ ወይም መረጃ

information's network and techniques of organized criminal groups.

## PART SEVEN
## Miscellaneous Provisions

### 44. International Cooperation

1/ The Ministry of Justice, when necessary in collaboration with Ministry of Foreign Affairs, shall cooperate with the competent authority of another country in matters concerning trafficking in person and smuggling of migrants, including the exchange of information, joint investigations, extradition and other legal cooperation in accordance with this Proclamation, agreements to which Ethiopia is a party and within the limits of the country's legal system; and serves as a central authority.

2/ The Ministry of Justice, as appropriate, may sign different international legal cooperation framework agreements with other countries to prevent the crime and to bring suspected offenders before law.

3/ For the implementation of this Proclamation, Police may exchange information based on principle of reciprocity with institutions of another country having similar mission, perform joint cooperation in other forms or sign memorandum of agreement with institutions of another country, when necessary.

4/ The non-conclusion of agreements specified in this Article, shall not preclude the Government from taking administrative measures in relation to the making and receiving requests of joint legal cooperation and assistance.

5/ Any information or evidence obtained pursuant to this Article shall only apply for the

ካልሆነ በስተቀር በዚህ አንቀጽ መሠረት የተገኘ ማንኛውም መረጃ ወይም ማስረጃ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከል ወይም ለመመርመር ዓላማ ይውላል፡፡

**፵፭. ንብረት ስለመውረስ**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ እና ፳፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠ በጥፋተኛው ላይ ከሚወሰኑ ቅጣቶች በተጨማሪ የወንጀል ፍሬ የሆነ ማንኛውም ንብረት እንዲወረስ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል አመንጪ ወንጀል ሆኖ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፯፻፹/፪ሺ፭ አንቀፅ ፴፭ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፵፮.ስለሌሎች ወንጀሎች**

ማንኛውም የመንግስት የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በዚህ አዋጅ ከተደነገጉት ወንጀሎች ውጭ በሌላ ሕግ የተደነገገን ወንጀል ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት ተጠያቂ የሆነ ሰው ሌሎች ተደራራቢ ወንጀሎችን የፈፀመ እንደሆነ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በተደራራቢነት የሚኖርበት የወንጀል ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ይሆናል፡፡

**፵፯. ስለውክልና**

ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል በህገ መንግስቱ ለክልል ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውክልና ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ እንደቅደም ተከተሉ ሚኒስቴሩ ወይም የፌደራል ፖሊስ በወንጀል ጉዳዩ ላይ ያላቸውን ስልጣን እንደአስፈላጊነቱ ለክልል ፍትህ ቢሮ ወይም ለክልል ፖሊስ ኮሚሽን በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

purpose of prevention or investigation of trafficking in human or smuggling of migrants, otherwise than used for any serious crime punishable with a severe penalty.

**45. Confiscation of Property**

1/ Without prejudice to Article 13 and 22 of this Proclamation, the court, in addition to the sentence imposed, may pass additional order for the confiscation of any property which is a proceed of crime.

2/ Without prejudice to the provision of sub article (1) of this Article, the crime of trafficking in human and smuggling of migrants shall be a predicate offense and Article 35 of the Anti-Money Laundering and Countering Financing of Terrorism Proclamation No. 780/2013 shall be applicable with respect to the confiscation of proceed of crime.

**46. Other Crimes**

Where any person or public official or civil servants commit crime other than those provided for under this Proclamation, the concurrent criminal liability shall be maintained.

**47. Delegation**

For the implementation of this Proclamation Without prejudice to the delegation given to regional courts according to the Constitution, the powers of Ministry or Federal Police on the crime may be delegated to the regional justice bureau or to the regional police.

**፵፰. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

፩/ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፪፻፵፫፣ ፭፻፺፮፣ ፭፻፺፯፣ ፭፻፺፰፣ ፭፻፺፱ እና ፮፻፴፭ ለዚህ አዋጅ ተፈፃሚነት የላቸውም።

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**፵፱. ደንብ የማውጣት ስልጣን**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

**፶. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

**48. Inapplicable Laws**

1/ under this Proclamation, Article 243, 596, 597, 598, 599 and 635 of the Criminal Code of the Federal Democratic Republic of Ethiopia are inapplicable.

2/ No law, regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

**49. Power to Issue Regulation**

The Council of Ministers may issue regulations to implement this Proclamation.

**50. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa this 17th day of August 2015.**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERA DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**